በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር

THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA MINISTRY OF FOREIGN AFFAIRS

ፕሬስ መግለጫ PRESSRELASE

# የአድዋ ፓን አፍሪካ ዩኒቨርስቲ የመጀመርያው ዓለም ዓቀፍ ጉባኤ በአድዋ ከተማ ይካሄዳል

የአድዋ ፓን አፍሪካ ዩኒቨርስቲ የመጀመርያው ዓለም ዓቀፍ ጉባኤ በአድዋ ሚያዝያ 15 እና 16 ቀን 2010 ዓ.ም "የፓን አፍሪካዊነት ተቋም መፍጠር፤ የመጀመርያው የአድዋ ፓን-አፍሪካ ዩኒቨርስቲ ጉባኤ" በሚል መሪ ቃል ይካሄዳል።



የአድዋ ፓን አፍሪካ ዩኒቨርስቲ አስተባባሪ ኮሚቴ ዛሬ በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ "የአድዋ ፓን አፍሪካ ዮኒቨርስቲ በእውቀት የተካነ ማህበረሰብ እንዲኖር ጥረት ያደርጋል፡፡ ይህ ማህበረሰብ ታሪኩንና ባህሉን ጠንቅቆ የሚያውቅ ህብረሰቡን በጥብቅ የሚደግፍና ጥቅሙን ያለመሰልቸት የሚያራምድ ብሎም የተባበሩት አፍሪካን ዕውን እንዲሆን ምንጊዜም የሚታትር ማህበረሰብ ማየት ነው፡፡ በተጨማሪም ማህበረሰቡ የራሱ ሰላም ያለውና ከሌላው ዓለም ጋር በሰላም ለመኖር የሚሻ እንዲሆን መሥራት ነው፡፡"

E-mail spokesperson@mfa.gov.et facebook @mfaEthspokesperson, Twitter @mfaEthspokesperson, YouTube https://www.youtube.com/channel/UCa_KUDpwCLMWyyQIjfilgZg ☎ 011-5-15 8928/011-5-53 6731 Fax 011-5-51-43-00
✉393 Addis Ababa,Ethiopia

በጉባኤው ከሚሳተፉት ውስጥ የኢፌዲሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ክቡር ዶ/ር አብይ አህመድ፣ የሩዋንዳው ፕሬዚዳንት ፖል ካጋሜ ፣ የዮጋንዳው ፕሬዚዳንት ዩዋሪ ሙሴቨኒ እና የቀድሞው የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትርክቡር አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ እንደሚገኙበት ኮሚቴው ጠቅሷል።

በተመሳሳይ የታወቁ የፓን አፍሪካዊነት ምሁራንና ተመራማሪዎች ከአፍሪካ ፣ከአውሮፓ፣ ከአሜሪካ፣ በጉባኤው ላይ ይሳተፋሉ ብለዋል፡፡ የጉባኤው ዋና ዓላማ ጉዳዩ የሚመለከታቸውን ግለሰቦች፣ ድርጅቶችና ሀገሮችን ጥረታቸውን በማቀናጀት የዮኒቨርስቲውን ራዕይ ሥራ ላይ ለማዋል እንሆነም በመግለጫው ተገልጿል።

እንደ ኮሚቴው መግለጫ ጉባኤው ከሚወያይባቸው ርዕሶች መካከል የዩኒቨርስቲው ንድፈ ሀሳብ፣ ዓላማዎቹ የትምህርቱ ዐይነትና የሕንፃዎቹን ዲዛይን እንዲሁም ዩኒቨርስቲውን የሚመሩ የቦርድ ዳይሬክተሮች ይመርጣሉ፡፡

**የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር**

**ቃል አቀባይ ጽ/ቤት**

**ሚያዝያ 5 ቀን 2010 ዓ.ም.**

E-mail spokesperson@mfa.gov.et facebook @mfaEthspokesperson, Twitter @mfaEthspokesperson, YouTube https://www.youtube.com/channel/UCa_KUDpwCLMWyyQIjfilgZg ☎ 011-5-15 8928/011-5-53 6731 Fax 011-5-51-43-00
✉393 Addis Ababa,Ethiopia